# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 183 ህዳር 7 2004 ገጽ 1

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት "ሽብርተኛ" ተብላችሁ የተፈረጃችሁ ወይም ነገ መፈረጃችሁ የማይቀር ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነት እና ለእውነት የቆማችሁ ዜጎች ሁሉ በአንድ ላይ ቆመን የአገዛዙን ፍፃሜ እንድናፋጥን ጥሪ ያደርጋል። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ኢፍትሃዊ አገዛዝ ያንገሸገሸው መምህር የኔሰው ገብሬ እንደ ቱንዚያዊው ሞሃመድ ቡአዚዚ ራሱን በእሳት አጋይቶ ገደለ

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል ህሊናው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ መሆኑን በመግልጽ የኔሰው ገብሬ የተባለ የደቡብ ተወላጅ እራሱን በእሳት አጋይቶ መግደሉን የግንቦት7 ድምጽ ሬዲዮን ጨምሮ ሌሎች በርካታ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

የኔሰው ገብሬ በመባል የሚታወቀው መምህር በዳውሮ ዞን በተርጫ ከተማ ለበርካታ አመታት ነዋሪ ሲሆን የወያኔው አገዛዝ ሆድ አደር የዞንና የወረዳ ምክር ቤት ባለስልጣናት ተብየዎች በአንድነት ተሰባስበው በቅርቡ በዋካ የተፈጠረውን ችግር በሚወያዩበት ወቅት፣ በራሱ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ ራሱን እያቃጠለ ወደ ስብሰባ አዳራሹ መግባቱ ታውቁአል።

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቱኒዚያ ሙሃመድ ቡአዚዝ በራሱ ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ ለቱኒዚያዊያን ብሎም ለሰሜን አፍሪቃዊያን የነጻነት ጮራን ከፈነጠቀ ወዲህ ተመሳሳይ ህዝባዊ አመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ መነሳቱ አይቀሬ መሆኑን በመገንዘቡ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች በህዝብ ላይ ማለቂያ የሌለው በደልን እየፈጸመ እንደሆነ በስፋትና በተደጋጋሚ ሲዘገብ መቆየቱ ይታወቃል።

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ሪፖርተሮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው መምህር የኔሰው ራሱን በዕሳት እያጋይየ ወደ አዳራሽ ውስጥ ሲገባ የተመለከቱት ለወያኔው አገዛዝ ያደሩ ሆዳም የክልሉ ባለስልጣናት በመደናገጣቸው ከመምህሩ ለመራቅ ጥረት ያደርጉ ነበር ብሎአል። ኢሳት በዘገባው የኔሰው ገብሬ በከተማው ውስጥ ከሚታወቁት በሳል ምሁራን መካከል አንዱ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚናገሩ ገልጾ "ፍትህ እና ዲሞክራሲ በሌለበት አገር መኖር ሰልችቶኛል፣ በዚህ ሁኔታ በህይወት መቀጠል አዳጋች ነው" በማለት ይናገር እንደነበር ገልጠዋል ብሉአል። ኢሳት አክሎም መምህሩ በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት ከስራ ተባሮ እንደነበርና ወደ ስራ ለመመለስ ያደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ እንዳልተሳካለትም ታውቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በዋካ ከተማ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ መርተዋል በሚል የሃሰት ክስ አንድ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አባት ከሀላፊነታቸው መባረራቸው ተዘገበ። ባለፉት 2 ቀናት ብቻ ከ80 በላይ ሰላማዊ ሰዎችም ታስረዋል

በአካባቢው ያለውን ጭቆና፣ የመልካም አስተዳዳርና የፍትህ መታጣት በመቃወም እራሱን በእሳት በማጋየት ተቃውሞን የገለጠው የመምህር የኔሰው ገብሬ አስደንጋጭ ዜና የህዝቡ የመነጋገሪያ አጀንዳ በሆነበት ማግስት፣ የአካባቢው ባለስልጣናት፣ "ተቃውሞውን የሚያስተባብሩት በከተማው የሚገኘው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ካህን ናቸው" በሚል ሰበብ፣ የቤተክርስቲያኑዋን አስተዳዳሪ የሆኑትን በኩረ ትጉህን ይልማ መኮንንን ከሃላፊነታቸው ማባረራቸውን ኢሳት ከትናንትና በስቲያ የዜና እወጃው ዘግቦአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ የእገዳውን ደብዳቤ የጻፉት የዞኑ የአገረስብከት ሀላፊ የሆኑት መምህር ወንዶሰን ክፍሌ ሲሆኑ፣ ለበኩረ ትጉሀኑ ከሀላፊነት መነሳት ምክንያት አድርገው ያቀረቡት "ሀይማኖትን ምክንያት በማድረግ መንግስትና ህዝብ እንዲጋጩ አድርገዋል" የሚል ነው።

በቁጥር ዳ/ ካሲ/ 322/ 2004፣ በቀን 24-02-2004 ለበኩረ ትጉሀን ይልማ መኮንን ከስራ እና ከደሞዝ መታገዳቸውን ስለማሳወቅ በሚል ርእስ በተጻፈው ደብዳ የሚከተለው ይዘት ሰፍሯል።

*"ግለሰቡ በመንግስታዊ ወይም ፖለቲካ አሰራር ጣልቃ ከመግባታቸውም በተጨማሪ ጉዳዩን ሀይማኖታዊ ሽፋን በመስጠት ህዝቡን እና ቤተክርስቲያንን ከመንግስት ጋር ለማጋጨት ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ የአንድ ሀይማኖት መሪ የሆነ ሰው የአካባቢውን ሰላምና አንድነትን የማስጠበቅ ሀላፊነቱን ወደ ጎን በመተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የአገሪቱን ሰላምን፣ ጸጥታን እንዲሁም የልማት አጋር በመሆን የነበራትን መልካም ስም እና ዝናን በአካባቢው ጥላሸት እንዲቀባ አድርገዋል፣ ስለሆነም ይህን ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት የምንሰጠው በመሆኑ ሀይማኖታዊ ፖለቲካ ስለማይኖረን አገረስብከቱ አስፈላጊውን ማጣሪያ አድርጎ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ከቀን 24-02-2004 ጀምሮ ከስራ ሀላፊነት ከማንኛውም አገልግሎትና ከደሞዝ የታገዱ መሆናቸውን እያስታወቅን የንብረት ርክክብ በቦታው ላለው ካህን እንዲፈጸም ሆኖ ከዛሬ ጀምሮ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን እንዳይወክሉ ለሁሉም አካላት በጥብቅ እናስታውቃለን"*

እገዳውን ተከትሎ የአካባቢው ፖሊስ ባለፈው እሁድ ወደ ቤተክርስቲያኑዋ በመሄድ መምህር ይልማ ንብረት እንዲያስረክቡ ሲጠይቁ፣ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኢትዮጵያዊው ሞሃመድ ቡአዚዚ አጭር ህይወት ታሪክ

የኔሰው ገብሬ ይባላል። ዕድሜው ወደ 29 አመት ነው። ሥራው መምህር ነበር።የተወለደው በጂማ ከተማ ዉስጥ ሲሆን የአንደኛም ሆነ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው እዚያው ጂማ ከተማ ነበር። ከዚያም ወደ ዋካ ከተማ በመምጣት ታላቅ እህቱ ዘንድ ኑሮዉን አደረገ። ከዚያም ወደ መምህራን ኮሌጅ በመግባት በመምህርነት



Ethiopian Bouazizi Yenesew Gebre

ሰልጥኖ በዳዉሮ ዞን ዉስጥ በተለያዩ ወረዳዎች ዉስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እየተዛወረ በመምህርነት አገልግሏል።

መምህር የኔሰው በመምህርነት ሙያው እጅግ የተከበረ ነበር። መጻህፍት ማንበብና እውቀቱን ለማስፋት የሚያደርገው ጥረት በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ የሚታወቅለት ባህርዩ ነበር። የቋንቋ ችሎታው ወደር አልነበረውም። የኔሰው የትኛዉን የትምህርት ዓይነት ነው የሰለጠነው? በሚባል መልኩ የሁለገብ እውቀት ባለቤት ነበር።

ከአንድ ወር ወዲህ የዳዉሮ ዋካ ህዝብ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ በየደረጃው ለመንሥስት አቅርቧል። እንዲሁም አላግባብ ግለሰቦች በሥልጣን ዘመናቸው ቦታ ተመርተው፣ ቤት ገንብተውና ነግደው ለመጠቀም ሲሉ ብቻ፤ የህዝብን አደራ ወደ ጎን በመተው የወረዳ አስተዳደር እርከን የነበራትን፣ አብዛኛውን የወረዳዉን ህዝብ የምታማክለዉን የዋካ ከተማ የወረዳ ርዕሰ ከተማነትን አሳጥተዋል። ስለዚህ ተግባራዊ የሆነ መፍትሄ ይሰጠን አለ ህዝቡ። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በዋካ በርካታ ሰዎች እየታሰሩ ነው፤ ወያኔ ለሚያካሂደው የአገር ሃብት ዘረፋ በመሳሪያነት እያገለገሉ ያሉ የአካባቢው ባለስልጣናት በእጅጉ መደናገጣቸው ተነግሯል

የዋካ ነዋሪዎች እንደሚሉት መምህር የኔሰው ገብሬ እራሱን በእሳት አቃጥሎ ከገደለ በሁዋላ፣ በከተማው ውስጥ አመጽ ሊያስነሱ ይችላሉ የተባሉ ከ80 ያላነሱ ሰዎች ባለፉት ሁለት ቀናት መታሰራቸውን ኢሳት በትናትናው ዜና ዘገባው ገልጾአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ እስካሁን ድረስ በተጫ ከተማ ብቻ ተወስኖ የነበረው እስር ወደ ገጠር መውረዱን የሚናገሩት ነዋሪዎች፣ የአካባቢው ባለስልጣናት ህዝቡን ለማሸበር መሳሪያቸውን ታጥቀው በከተማው እየተዘዋወሩ እንደሚገኙና ለራሳቸውም በከፍተኛ ደረጃ እንደተረበሹ ታውቆአል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት ይሰራሉ ተብለው ከስራ እንዲታደጉ የተደረጉት የኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን ሃላፊ የሆኑት በኩረ ትጉህን ይልማ መኮንን የቀረበባቸውን ክስ ማስተባበላቸው ተዘግቦአል።

በኩረ ትጉህን ይልማ እርሳቸው እንደማንኛው የአካባቢው ነዋሪ በግል የሙብት እና የልማትጥያቄዎችን ከማንሳትናቤተክርስቲያኑዋእንዳትዳከምና እንዳትደፈር ከማከላከል ውጭ በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ አልመግባታቸውን ለኢሳት ተናግረዋል።

የቤተክርስቲያንቷን ሃላፊ ከስራ ያገዱዋቸው የዞኑ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ የሆኑት መምህር ወንዶሰን ክፍሌ ግን በኩረ ትጉህን ይልማ ከስራ የታገዱት በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ በመግባታቸው እንደሆነ እራሳቸው ለኢሳት በሰጡት ቃል እንዳረጋገጡ ለማወቅ ተችሎአል።

በዋካ ዞን በዳውሮ ቶርጫ የተነሳው ውዝግብና የመምህር የኔሰው ገብሬ ሞት በኢትዮጵያ ውስጥ የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆነ በመጣበት በአሁኑ ሰዓት በዘረኛው ወያኔ ሥር የሚተዳደሩ የሚዲያ ተቋማት ኢፍትሃዊነትን ተቃውሞ ህይወቱን በ እሳት ያጋየውን አርበኛ መስዋዕትነት ለማጣጣል መምህሩ የአይምሮ በሽተኛ የነበረ ነው ሲል ማስተባበሉ ተዘግቦአል።

ከወያኔ ልሳኖች አንዱ የሆነው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል በትናትናው ዕለት በባለሥልጣናቱ የተፈቀነባበረ የሃሰት ህክምና ማስረጃ በማያያዝ በድህረ ገጹ ላይ ባወጣው ሪፖርት ሟቹ መምህር የኔሰው ገብሬ ህይወቱን ያጠፋው የአ እምሮ በሽተና ስለሆነ ነው ብሎአል። ለዚህም የሃሰት ማስተባቢያው በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሰዎችን እንዳነጋገረና ገልጾአል። በተጨማሪም የቶርጫ ወረዳ ሆስፒታል ዋና ስራአስኪያጅ ነው የተባለ ግለሰብ ምስክርነት ለንባብ አብቅቶአል። ዋልታ ኢንፎርመሽን መምህር የኔሰው በኢሳት ቃጠሎ ሆስፒታል በገባበት ወቅት ህክምናውን የሰጡትን ዶክተር ከማናገር ይልቅ ለምን ከሙያው ጋር ምንም ግንኙነት ከሌለው የሆስፒታሉ ሥራአስኪያጅ ጋር ቃለመጠይቅ ለማድረግ እንደፈለገ የተሰወረ አይደለም።

በዋካ በተነሳው ህዝባዊ አመጽ እጅግ የተደናገጠውና የመምህር የኔሰው አር አያነት በሁሉም ስፍራ እንዳይሰራጭ ስጋት የገባው የወያኔ አገዛዝ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከመለስ ዜናዊ ክስ መረዳት የሚኖርብን ሃቅ!

የኢትዮጵያን ፍርድ ቤቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉት የመለስ ዜናዊ ካድሬዎች ሰሞኑን የተለመደ ድራማቸውን አጧጡፈዋል። የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ በሆኑት በአቶ አንዱዓለም አራጌ መዝገብ ውስጥ ሃያ አራት ዜጎች በበርካታ የፈጠራ የሽብር ወንጀሎች ተከሰዋል። ከተከሳሾቹ ስምንቱ ብቻ ናቸው በመለስ መዳፍ ውስጥ ያሉት። ሌሎቹ የገቡት ለማዳመቂያና ለማስፈራሪያ ነው።

አስራ ሰባት ገፆች ያሉት "የክስ ቻርድ" የተሰኘው ጦማር በየገጹ ሥር ከሚገኘው "ፍትህ በተለወጠ አመራር፤ በተለወጠ ሠራተኛ፣ በተለወጠ ተቋም" ከሚል አዝናኝ፣ አስቂኝና አስገራሚ መፈክር በስተቀር በይዘቱ ከምርጫ 97 ጀምሮ ከምናውቃቸው ተመሳሳይ እንቶ ፈንቶ ድርሳናት የተሻለ ነገር የለበትም።

በተከሳሽነት የተዘረዘሩት ዜጎችም ያው የተለመዱ ወገኖች ናቸው:

- ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የቆሙ የፓለቲካ ፓርቲዎች መሪዎችና አባላት፣
- የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣
- እውነትን ለመዘገብ የደፈሩ ጋዜጠኞች፣ እና

የማይታወቁ ሰዎች ናቸው፣

በምርጫ 97 ማግስት የወጣው የክስ ዝርዝርም የያዘው እነዚሁኑ ወገኖች ነበር።

ያም ሆኖ ግን ይህን ክስ ከዚህ በፊት ከነበሩት ተመሳሳይ ክሶች በሁለት አበይት ነገሮች ይለያል። እነዚህም:-

1. ተከሳሾች በሙሉ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አመራርና አባላት ናቸው መባላቸው፤ እና
2. ህገ-አልባነትን ህጋዊ ያደረገው "የፀረ- ሽብር" ህግ ተጠቅሶ የተከሰሱ መሆናቸው ናቸው።

እነዚህ ሁለት ነጥቦች በጥልቀት መጤን ያለባቸው ነገሮች ናቸው።

ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነት እና ለእውነት የቆመ ኢትዮጵያዊ የየትኛውም ድርጅት አባል ቢሆን፣ ወይም ደግሞ የማንኛውም ድርጅት አባል ባይሆን፣ ለመለስ ዜናዊ ለውጥ የለውም። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ባለችው ኢትዮጵያ ማንኛውም ለመብትና ለእውነት የቆመ ኢትዮጵያዊ በግንቦት 7 አባልነት ተፈርጆ በሽብርተኝነት ሊከሰስ ይችላል።

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነት እና ለእውነት የቆምን ዜጎች ሁሉ ትግላችንን ማስተባበር እንዳለብን የሚጠቁም ነው። ይህ በመካከላችን ያሉ ትናንንሽ ልዩነቶች ከትላልቆቹ ግቦቻችን አንፃር ሲታይ ቦታ የማይሰጣቸው መሆኑ ጎልቶ የታየበት ክስተት ነው። ይህ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተደረገ ጥሪ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ክስ፣ "የፀረ-ሽብር ህግ" ተብሎ የሚጠራው የመለስ ፓርላማ ውሳኔ በህግ፣ በህጋዊነትና በፍትህ ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት አጉልቶ የሚያሳይ ነው። በዚህ "ህግ" ምክንያት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አንዳችም የደህንነት ዋስትና የሌለው መሆኑ ይህ ክስ አረጋግጧል። ህግ የግለሰቦች መጫወቻ በሆነበት አገር ተፈርቶም ሆነ ተሸሽጎ የሚመለጥ ነገር የለም።

ህግ የግለሰቦች መጫወቻ በሆነበት አገር በቅድሚያ መፈጸም ያለበት ተግባር ህጋዊ ሥርዓትን ማቆም ነው። ህጋዊ ሥርዓት ሳይኖር ስለምንም ሌላ ነገር (ለምሳሌ ስለ ተለያዩ ፖሊሲዎች) መናገር ፋይዳ የለውም። በአገራችን ህጋዊ ሥርዓት ማቆም ማለት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ ቡድን ከሥልጣን ማባረር ማለት ነው። ይህ ተግባር ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊ ጉዳይ እንደሆነ ክሱ በሚገባ አረጋግጧል።

ስለሆነም ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት "ሽብርተኛ" ተብላችሁ የተፈረጃችሁ ወይም ነገ መፈረጃችሁ የማይቀር ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነት እና ለእውነት የቆማችሁ ዜጎች ሁሉ በአንድ ላይ ቆመን የአገዛዙን ፍፃሜ እንድናፋጥን ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## የኢትዮጵያዊው ሞሃመድ ቡአዚዚ አጭር ህይወት ታሪክ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መምህር የኔሰው ሳይሆን ጥያቄዉን ያቀረበው፣ ያመፀው፣ አደባባይ የወጣው የዋካ ከተማና አካባቢው ነዋሪ ህዝብ ነው። አቤቱታ ለበላይ አካል አቅርባችሁብናል፤አሳጣችሁን፤ የሥልጣን ዕድሜያችንን አሳጠራችሁብን፤ አርፋችሁ ለምን አትገዙልንም... የሚሉ ባልሥልጣኖች የህዝብ ተወካይ የሆኑትን ያገር ሽማግሌዎችን በሙሉ ሰብስበው አሰሩ። አመጹን አቀጣጥላችሁታል በሚል በርካታ ወጣቶችም ታጎሩ። መምህር የኔሰውም አስተባባሪ ነበርክ በሚል ብቻ ያለአንዳች መረጃ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር በቁጥጥር ሥር እንዲቆይ ተደርጎ፤ ምንም መረጃ ሊቀርብበት ባለመቻሉ ከሽማግሌዎች ጋር አብሮ ተፈቷል።

የሰዉ በደልና ስቃይ የሚያመው፤ ለፍትህና ለነፃነት የቆመ፤ ሁልጊዜ በየመድረኩ ስለ ዴሞክራሲና እኩልነት ይሚዘምር አገር ወዳድ ወጣት ነበር መ/ር የኔሰው። በኢትዮጵያ ዉስጥ የተንሰራፋው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲወገድ፤ ያለአግባብ በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀመው እስር፣እንግልት፣ዱላ የመሳሰሉ ነገሮች እንዲቆሙ፤ በየደረጃው የሚገኙት ባልሥልጣኖች የህዝብ ወገንተኝነት እንደሚጎድላቸው በአንክሮ ተናግሯል።

በ2011-11-11 ማለትም ባለፈው ዓርብ ዕለት በእስር ቤት የነበሩት ጓደኞቹ ፍርድ ቤት የሚቀርቡበት ቀን ነበርና ሁኔታዉን ለመከታተል መ/ር የኔሰውም ማረቃ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀረበ። አላግባብ ታስረው ስለነበር ይፈታሉ የሚል ግምት ህዝቡ ነበረው። ለካስ ዳኛው ፍታቸው ተብለው አልታዘዙ ኑሯል። ሌላ የጊዜ ቀጠሮ ይሰጣሉ ዳኛው። መቼም ዳኛ ናቸው እንበልና ነው።

በዚህ ሁኔታ ፍርድ ቤት ቀርበው ሲከታተሉ የነበሩ የእስረኞቹ ቤተሰቦች በጣም ገርሟቸው ታሳሪዎቹን አይዟችሁ ምንም አትሆኑም፤ ጀግኖቻችን ናችሁ፣ ነገ ይህ ቀን ታሪክ ይሆናል ብለው አፅናንተዋቸው ታሳሪዎቹ ወደ ወህኒ ቤት ወረዱ። ከዚህ በኋላ ነው መ/ር የኔሰው በሃገሪቱ እውነትና ፍትህ እንደሌለ፤ ነፃነትና ዴሞክራሲ በዚህ ሥረዓት በፍፁም የማይታሰቡ ነገሮች መሆናቸው ፍንትው ብሎ የታየዉና ለነፃነት ትግሉ ወጣቱ ትውልድ አርማዉን እንዲያነሳ አሳስቦ ራሱን ለመሰዋት የወሰነው።

በህይወቱ ላይም ዉሳኔ የሰጠው እነዚህና የመሳሰሉትን በደሎች በሌላው የህብረተሰብ ክፍል ላይ መፈፀሙ ተገቢነት እንደሌለው በአንክሮ ስለሚያምን ነበር። እውነተኛ የህዝቡን ልጆች ያለምክንያት አሰሩዋቸውት። እሱ ቀድሞ ከእስር በመፈታቱ ምክንያቱን ጠየቃቸው። እንኳንና የታሰረበትን ምክንያቱን ሊነግሩት ቀርቶ ያሰረህ ይሄ ክፍል ነው፣ ወይም እኔ ነኝ፤ የሚል አካል ማጣቱ እጅግ አንገበገበው።

ከዚያም ከፍ/ቤት ምልስ ጉዞዉን ወደ አስተዳደር ጽ/ቤት አደረገ። እሱ አስተዳደር ጽ/ቤት ግቢ ሲደርስ ከፍተኛ የክልል ባለሥልጣኖችን ጨምሮ የዳዉሮ ዞን አመራሮች፤ የሁሉም ወረዳ አስተዳደር ተወካዮች በሚወያዩበት ቀርቦ፤ አለምክንያት እንደእንስሳ መታሰሩ ሳያንስ ያሰረዉን አካል እንኳ ለማወቅ መብት ማጣቱ እጅግ እንዳንገበጋበው፤ በዚህ ሥርዓት እንኳንና የግለሰብ የህዝብ ነፃነት ብሎ ነገር እንደሌለ ማረጋገጡን፤ ለልማት ሳይሆን የሚወያዩት ህዝብንና አገርን ለመበደል ብሎም ራስን ማገልገል የዘወትር ተግባራቸው መሆኑን፤ ህዝብ ነፃነት እንደሌለው ማረጋገጡን በኃይለ ቃል ከተናገረ በኋላ፤ የዋካ ከተማ ህዝብ በአመፅ ወቅት በአደባባይ ሲያስተጋባ የነበረዉን መፈክር እንደገና ብቻዉን አስተጋባ።

ከዚያም አስተዳደር ጽ/ቤቱ ግቢዉን ሳይለቅ ቢሮው በራፍ ላይ ብዙ ሰዎች እያዩት ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ ክብሪት ጭሮ ራሱን በእሳት ለኮሰው። በአቅራቢያው የነበሩ ሰዎች በንግግሩና በመፈክሩ ተመስጠው ያዳምጡት የነበሩ ሁሉ አዝነውና ደንግጠው እሳቱን ለማጥፋት ሣር፣ቅጠል፣ አፈር፤ ውሃ ያገኙትን ሁሉ ተጠቀመው እሳቱን በማጥፋት እሱን ለማትረፍ ተሯሯጡ።

ህክምና እንዲያገኝ ወደ ተርጫ ሆስፒታል ቢወስዱትም የኔሰው ገብሬ አልተረፈም። ትናንት ሰኞ ቀን ረፋዱ ላይ በሆስፒታሉ ዉስጥ ህይወቱ አልፏል። የዳዉሮው የነፃነት አርበኛ መ/ር የኔሰው ገብሬ ለዴሞክራሲና ለፍትህ እንዲሁም ለህዝብ የበላይነት ሲል እነሆ ሁለተኛው ሞሃመድ ቡዐዚዝ ሆነ። በዚህ ዓይነት ከዋካ የተነሳው እሳት የት ይደርስ ይሆን? እንጠብቅ!

## በዋካ በርካታ ሰዎች እየታሰሩ ነው፤ ወያኔ ለሚያካሂደው . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የዳውሮ ዞን አስተዳዳሪ አድርጎ የመደበውን እስራኤል አታራ የተባለ ግለሰብ ኢንተርቪው በማድረግ እውነተኛውን ዜና ለህዝብ ጆሮ እያደረሱ ያሉትን ኢሳትና የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ክፍል እንዲያወግዝና ከማድረግ አልፈው "የኢትዮጵያን ህዝብ ለማተራመስ ከያዙት አጀንዳ እንዲቆጠቡ"በማለት ማሳሰቢያ እንዲሰጥ እንዳደረጉት ተዘግቦአል።

የዳውሮ ዞን አስተዳዳሪ ተብዬው ይህ ግለሰብ "ኢትዮጵያ ውስጥ አመጽና ሽብርተኝነትን ለማስፋፋት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአሸባሪነት የተፈረጁ ቡድኖች የተዛባና የሀሰት ዘገባዎችን በማሰራጨት በህዝቡ ላይ ውዥንብር ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት ዋጋ የለውም እንዳለና በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን ህዝብ ለአመጽ የሚቀሰቅስ ጥሪ ሲያቀርቡ ህዝቡ በበኩሉ ጆሮውንም ልቡንም ስለነፈጋቸው የሟች የኔሰውን አሟሟት ከቱኒዚያው ወጣት ጋር ለማመሳሰል ያደረጉት ጥረት ቀቢጸ ተስፋቸውን እውን ለማድረግ የተጠቀሙት ዘዴ መሆኑን ማንም መረዳት አያዳግተውም ብሎ መናገሩን ዋልታ ገልጾአል።

ከሁሉም የሚገርመው አብዛኛው የአገራችን ወጣትና ጎልማሳ አገሪቱ ውስጥ በተስፋፋው ኢፍትሃዊነትና ድህነት ተማሮ አገሩን ጥሎ እየተሰደደ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ በሃብት ዘረፋ የከበሩ የወያኔ መሪዎች በራሳቸው ድሎትና ምቾት አገር እየመዘኑ ስለልማትና እድገት፤ ፍትህና ብልጽግና በሚደሰኩሩት ባዶ ፖርፖጋንዳ እራሳቸውንና ጀሌዎቻቸውን አሳምነው አገራችን ውስጥ ህዝባዊ አመጽ የሚቀሰቅስ ችግር የለም ሲሉ መስተዋላቸው ነው። ለዚህም ይመስላል ወያኔ በቶርጫ የመደበው አስተዳዳሪ አገራችን ውስጥ እየተቀጣጠለ ያለውን ተቃውሞ ለማጣጣል ሲናገር "በመላው አለም የተከሰተውን የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና በተለይ በአረቡ ሀገራት ለዘመናት ስር ሰዶ የቆየውን ንጉሳዊ ስርዓትና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ከሚቃወሙ ህዝቦች ጋር ኢትዮጵያን ማመሳሰል አላዋቂነትና ሀገሪቱም እንዲህ ያለውን የእርስ-በርስ ግጭት ከ20 አመታት በፊት እንዳለፈችው ያለመረዳት ውጤት ነው ያለው።

ዋልታ ዘገባውን ያጠናቀቀው "ለርካሽ ፖለቲካ ጠቀሜታ ሲሉ እውነትነትን የሌለውን መረጃ በማሰራጨት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የተረጋጋ ፖለቲካ ለማደፍረስ የሚፈልጉ በውጭ ያሉ ሚዲያዎች በተለይም ኢሳትና ቪኦኤ ከእንደዚህ አይነት ድርጊታቸው እንዲታቀቡ የዳውሮ ዞን ዋና አስተዳዳሪና የሟች ቤተሰቦች አስጠንቅቀዋል በማለት ነው። ሆኖም ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል በዋካ ከተማ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለማስተባበል አልደፈረም።

ኢሳት የመንግስት ባለስልጣናት ሟቹ የአእምሮ በሽተኛ ነው ብላችሁ በሉ በማለት ነዋሪዎችን ሲያዋክቡ እንደነበር ቀደም ብሎ ዘግቦ እንደነበር አይዘነጋም።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሲረገጥ የሚታገስ ሲጫኑት የሚሸከም መሬት ብቻ ነዉ!

የኢትዮጵያን ህዝብ ከተቀረዉ የአፍሪካ ህዝብ ከሚለዩት ዋና ዋና ባህሪዮች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ለአገሩ ዳር ድንበር፤ ለመሬቱና ለሐይማኖቱ የሚሰጠዉ ልዩ ቦታ ነዉ። ይህንን ልዩ ባህሪዩን ደግሞ እንኳን ወዳጆቹ ጠላቶቹም በዉል ተገንዝበዉለት ሳይወዱ በግድ በታሪክ መዝግበዉ ያስቀመጡትና ቢፍቁት ቢፍቁት የማይደበዝዝ ሃቅ ነዉ። የቀድሞዉ መሪዎቻችን ህዝቡ አገሩንና አንድነቱን ከወራሪ እንዲከላከል ጥሪ ሲያደርጉ አገርህን ሊቀማህ፤ መሬትህን ሊወርስና ሐይማኖትህን ሊያረክስ የመጣብህን ጠላት ለመከላከል ዛሬ ነገ ሳትል ተከተለኝ እያሉ ነበር። ለኢትዮጵያ ህዝብ መሬት የኤኮኖሚ ኃብት ብቻ ሳይሆን የባህሉ መገለጫ፤ የጥንት አባቶቹ ቅርስ መተላለፊያ፤ የዜግነቱ ዋስትናና የህልዉናዉ መሠረት ነዉ። ስለሆነም ኢትዮጵያ  የምትባል አገር በታሪክ ታዉቃ መኖር ከጀመረችበት ግዜ ጀምሮ ኢትዮጵያዉያን መሬታቸዉን በየዘመኑ ከመጣ ጠላት ሲከላከሉ ቆይተዉ ዛሬ ላይ ደርሰዋል። ባለፉት ሃያ አመታት ወያኔ እራሱ ጭሮ ካመጣዉ ችግር ዉጭ አገራችንን የወረረ የዉጭ ኃይል የለም። ሆኖም እኛ ኢትዮጵያዉያን አንድነታችንን፤ መሬታችንን፤ ሐይማኖታችንንና ሰብዓዊ ክብራችንን በተመለከተ "ነፃ አወጣናችሁ" የሚሉን የወያኔ ዘረኞች ያደረሱብን በደል አንዳንዴ የዉጭ ጠላት ምን አደረገን የሚያሰኝ ነዉ።

የወያኔ መንጋ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ትኋን ተጣብቶት ኃብቱንና ቅርሱን መቦጥቦጥ የቻለዉ የገበሬዉን መሬት የራሱ ንብረት ማድረግ በመቻሉ ነዉ። ወያኔ የጻፈዉ ህገ መንግስት መሬት የመንግስትና የህዝብ ንብረት ነዉ ይላል፤ ሆኖም የወያኔን ፀባይና አገራችን ዉስጥ ምላሽ ያላገኘዉን የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ የተገነዘበ ማንም ሰዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት የህዝብና የመንግስት ሳይሆን የወያኔ የግል ንብረት መሆኑን በሚገባ ያዉቃል።  ብዙ አለም አቀፍና የአገር ወስጥ የእርሻ ጠበብቶች የኢትዮጵያ ገበሬ የመሬቱ ባለቤት ካልሆነ ኢትዮጵያ ከድህነትና ከጥገኝነት አትላቀቅም ብለዉ በተደጋጋሚ ወያኔን መክረዋል። ይህንን የአዋቂዎች ምክር ጆሮ ዳባ ልበስ ያለዉ ወያኔ ግን ከድጡ ወደማጡ እንዲሉ ጭራሽ የከተማዉንም መሬት ከባለቤቱ ቀምቶ የራሱ ለማድረግ ከህዝብ ጋር ግብግብ ተያይዟል። ወያኔ አዲሱ የመሬት አዋጅ የመሬትን ባለቤትና ተጠቃሚ መብትና ግዴት ያረጋግጣል ብሎ ህዝብን ለመደለል ቢሞክርም የአዋጁ አላማ ግን ከተሜዉን መሬት አልባ በማድረግ ይህንን ጧትና ማታ እረፍት የነሳዉን ህብረተሰብ እጅና እግሩን አስሮ ጭጭ ለማሰኘት ነዉ። የኢትዮጵያን ህዝብ ወያኔ ይህንን ከሰሞኑ ያወጀዉን የከተማ መሬት አዋጅ ተግባራዊ ሲያደርግ ዝም ብሎ ከተመለከተ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ የገጠሩ አርሶ አደርና የከተማዉ ሥርቶ አደር መሬት አልባ ይሆናሉ። እንግዲህ የኢትዮጵያ ህዝብ መሬት አልባ ሆነ ማለት ደግሞ ከታሪኩ፤ ከባህሉ፤ ከአባቶቹ ቅርስና ፈጣሪ ከሰጠዉ ንብረቱ ጋር ተላቀቀ ማለት ነዉ። ይህ የዛሬዉን ትዉልድ ብቻ ሳይሆን መጪዉን ተከታታይ ትዉልድ ደግሞ ደጋግሞ የሚገድል የወያኔ ሴራ በተግባር ሲተረጎም የኢትዮጵያ ህዝብ ዝም ብሎ ይመለከታል የሚል ብዥታ የለንም። ሆኖም በዚህ በታሪካችን እጅግ በጣም ወሳኝ በሆነ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ወጣት፤ ሽማግሌ፤ ሴትና ወንድ ሳይል ሃያ አመት ሙሉ እምቆ ያቆየዉን ህዝባዊ ቁጣ አሁን ካልተወጣዉ ሌላ ከዚህ የተሻለ ግዜ ሊመጣ እንደማይችል ከማስጠንቀቅ ወደኋላ አንልም።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ኢትዮጵያ ዉስጥ አዲስ የመሬት ባለቤት፤ አዲስ የፋብሪካ ባለኃብት፤ አዲስ የቢዝስ ህብረተሰብና በአጠቃላይ አዲስ የከበርቴ መደብ ለመፍጠር በብሔራዊ ደረጃ ዕቅድ አዉጥቶ መንቀሳቀስ ከጀመረ አመታት የተቆጠሩ ሲሆን በተለይ ከ1997 ዓም ጀምሮ ይህንን ዕቅዱን ተግባራዊ  ለማድረግ ጥድፊያዉን ተያይዞታል። መለስ ዜናዊ በ1997ቱ ምርጫ የደረሰበትን ሽንፈት አልቀበልም ማለቱ ብቻ ሳይሆን ድምፄ ይከበርልኝ ብሎ መብቱን የጠየቀን ህዝብ በጭካኔ መጨፍጨፉ ምንግዜም ቢሆን የማይረሳን መጥፎ ትዝታ ነዉ። የሚገርመዉ መለስ ዜናዊ በ1997ቱ ምርጫ የደረሰበትን ሽንፈት የሚያላክከዉ በራሱ ምግባረ ብልሹነትና አምባገነንነት ላይ ሳይሆን "የደርግ ርዝራዥ" እያለ በሚጠራዉ የከተማዉ ነዋሪ ህዝብ ላይ ነዉ። ከዚህ በመነሳት ይመስላል ወያኔ የከተማዉን ነዋሪ ህዝብ ለመበቀል የከተማ መሬት ሊዝ የሚል አዲስ አዋጅ በማወጅ በህግ ሽፋን ከተሜዉን ኢትዮጵያዊ መሬት አልባ ለማድረግ ቁጭ ብድግ ማለቱን የጀመረዉ። ወያኔ ይህንን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘምና ዬኔ የሚላቸዉን ሁሉ የመሬት ባለቤት ለማድረግ ያወጀዉን አዋጅ ፍትሃዊ አዋጅ እያለ ህዝብን ለመሸንገል ቢሞክርም የአዋጁ ዋና አላማ ከተሜዉን መሬት አልባ በማድረግ ይህንን ጧትና ማታ እረፍት የነሳዉን ህዝብ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ነዉ።

ወያኔ እያንዳንዱን የገጠር ነዋሪ "ምን በላህ" እና "ምን ጠጣህ" ብሎ መጠየቅ በሚያስችለዉ ደረጃ መቆጣጠር የቻለዉ የገጠሩ ህዝብ የደም ስር የሆነዉን መሬት ሙሉ በሙሉ መዳፉ ዉስጥ ማስገባት በመቻሉ ነዉ። የወያኔ መሪዎች የመሬት በመንግስት ይዞታ ስር መሆን የሚጠቅመዉ ገበሬዉን ነዉ ብለዉ ቢወተዉቱም እንደዚህ አይነቱ የመሬት ይዞታ የወያኔን በጠመንጃ የተያዘ ስልጣን ከማራዘም አልፎ ደሃዉን የኢትዮጵያ ገበሬና ሠራተኛ ጠቅሞ አያዉቅም ለወደፊትም አይጠቅምም። የወያኔ ካድሬዎች በየገጠሩ እየዞሩ እኛን ካልመረጥከን ከቤት ንብረትህ ትፈናቀላለህ፤ ማዳበሪያ፤ ምርጥ ዘርና የብድር አገልግሎች አታገኝም እያሉ በማስፈራራት ፓርቲያቸዉ በሚገርም ሁኔታ 99.6% የፓርላማ መቀመጫ እንዲያሸንፍ ማድረግ የቻሉት የገጠሩ መሬት የፓርቲያቸዉ ንብረት በመሆኑ ነዉ። አመፀኛዉ መለስ ዜናዊ ግን በዚህ የረካ አይመስልም፤ ስለሆነም የ1997ቱ ዉጤት በምንም መልኩ እንዳይደገም የከተማዉን ህዝብ ልክ እንደገጠሩ አርሶ አደር ከመሬቱ አፈናቅሎ የህወሀት ጥገኛ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል።

እንደ ታማኝ ፈረስ በመለስ ዜናዊ ልጓም ተለጉሞ ግራና ቀኝ የሚዘለዉ የኢትዮጵያ ፓርላማ በቅርቡ እወክለዋለሁ የሚለዉን የከተማ ነዋሪ ህዝብ ከመሬቱና ከቤቱ ነጥሎ ንብረት አልባ የሚያደርግ አዲስ አዋጅ አጽድቋል። ይህ አዋጅ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነዉ ወያኔ በጠመንጃ የጨበጠዉን ሥልጣን ዘለአለማዊ ለማድረግ ካቀዳቸዉ ዕቅዶች አንዱ ነዉ። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በዉል እንዲገነዘበዉ ከወዲሁ እንዲያስብበት የምንፈልገዉ እጅግ አደገኛ የሆኑ ብዙ የሆኑ የወያኔ ዕቅዶች አሉ። እነሱም:-

**አንደኛ**- ወያኔ በጋምቤላ፤በኦሮሚያ፤በቤንሻንጉልና በሌሎችም የተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መሬትን ከባለቤቱ ነጥሎ ለባዕዳን በመሸጥና በማከራየት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ባለቤትነት የማይሰማዉና ወያኔን እንዳከበረ የሚኖር ለአካባቢዉ ባዕድ የሆነ የመሬት ባለቤት መደብ እየፈጠረ ነዉ። የዚህ ሴራ ዋነኛዉ አላማ ደግሞ ገበሬዉን የወያኔና የዚህ በመፈጠር ላይ ያለ ባዕድ ባለ ኃብት መደብ ጥገኛ በማድረግ ከመብቱና ከነፃነቱ ይልቅ "ከእጅ ወደ አፍ" ወደሆነ ኑሮዉ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ ነዉ። ዛሬ ወያኔ ይህንን በገጠር የጀመረዉን የመሬት ቂሚያ በከተማዉም ለመጀመር አዋጅ አዉጇል።

**ሁለተኛ**- ወያኔዎች ባለፉት ሃያ አመታት አፎርት የሚባል በኢትዮጵያ ህዝብ ደምና እምባ የተገነባ የኤኮኖሚ መዋቅር በመገንባት መለስ ዜናዊ "ወርቃማዉ  ዘር" እያለ በሚጠራዉ የአንድ አካባቢ ሰዎች ብቻ የሚመራ እጅግ በጣም ግዙፍ የሆነ ባለ ኃብት መደብ ፈጥረዋል። ይህ መለስ ዜናዊ ሆን ብሎ ጠፍጥፎ የሰራዉ መደብ ደግሞ ካለመለስ ዜናዊ እራሱን ችሎ መቆም ስለማይችል የመለስ ዜናዊን ስርአት የሚቃወሙትን ኃይሎች ሽንጡን ገትሮ ከመዋጋት ወደኋላ የሚል አይደለም።

**ሦስተኛ** - ባለፉት አስር አመታት ዉስጥ ትምህርታቸዉን ጨርሰዉ ወደ ስራ አለም ለተሰማሩትና ኤፎርትን የመቀላቀል ዕድል ላላገኙ የትግራይ ገዢ መደብ አባላትና ቤተሰቦቻቸዉ ሌላ አዲስና ረቂቅ የሆነ የገንዘብና የንብረት መዝረፊያ መንገድ ተዘጋጅቷል። ይህ ወያኔ አዲስ መጥ ጓዶቹን ለማበልጸግ የቀየሰዉ ዘዴ ቀንና ማታ ሰርቶ ለልጆቹ የቋጠረዉን አብዛኛዉን ኢትዮጵያዊ የሚያደኽይ ነዉ። ለምሳሌ በአገራችን ታይቶ የማይታወቀዉ የሸቀጥ ዋጋ ንረትና መቆሚያ ቦታ ያጣዉ የብር ዋጋ መዋዠቅ ወያኔ የፀና ኢትዮጵያዊነት ስሜት ያላቸዉን ባለኃብቶች እያቀጨጨ ባምሳያዉ የፈጠራቸዉን አዲስ ባለኃብቶች የሚያፋፋበት የረቀቀ ዘዴ ነዉ። ሌላዉ ወያኔ የአገራችንን አንጡራ ኃብት በጉጅሌዎቹ ከሚያስዘርፍበት መንገድ አንዱ በጉምሩክ መስሪያ ቤቶች በኩል የሚደረገዉ አይን ያወጣ ዝርፊያ ነዉ። ጉዳዩ እንደዚህ ነዉ። የጉምሩክ መስሪያ ቤት ለአገር ግንባታ ስራ በሚል ሽፋን ለተወሰነ ግዜ የልማት ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ አገር ቤት ማስገባት እንደሚቻል የዉስጥ መመሪያ  ያወጣል። መመሪያዉ የዉስጥ መመሪያ ይባል እንጂ  የመመሪያዉን መዉጣት የሚያዉቁት ወያኔ ዬኔ የሚላቸዉና ከዉስጥም ዉስጥ የሆኑ የወያኔ እልፍኝ አስከልካዮች ብቻ ናቸዉ። እነዚህ የወያኔ እልፍኝ አስከልካዮች  ለአገር ልማት ጠቀመም አልጠቀመ ያሰኛቸዉን ያክል ዕቃ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ዉስጥ ካስገቡ በኋላ ህግ አክባሪዉ ነጋዴ በቀረጥ ነፃዉ ንግድ መሳተፍ ሲጀምር ግዜዉ አልፏል ተብሎ ይባረራል።  ዛሬ በዚህ አይነቱ ወገናዊ አሰራር በሚሊዮንና በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያካበቱ ወያኔ ሠራሽ ነጋዴዎች ቁጥር የትየለሌ ነዉ።

ለመሆኑ ወያኔ እነዚህን የኢትዮጵያ ህዝብ በቃ ያላቸዉን የኤኮኖሚና የፖለቲካ ፖሊሲዎች ህዝብ አናት ላይ እንደ ጫና የሚጭነዉ ለምንድነዉ ? መልሱ ቀላል ነዉ። ጥያቄዉን ለመመለስ ብዙ መመራመር የሚያስፈልግም አይመስለንም። የህወሀትን በተለይም የመለስ ዜናዊን የኋላ ታሪክ መለስ ብሎ መመልከቱ ይበቃል። መለስ ዜናዊ አብዛኛዉን የወጣትነት ዘመኑን የኖረዉ ጫካ ዉስጥ ነዉ፤ ይህ የጫካ ሰዉ ቤ/ክርስቲያኑ አልባኒያ ጥምቀቱ ማርክሲዝም ሌኒንዝም ነዉ። መለስ ዜናዊ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተግባር የሚተረጉማቸዉ ፖሊሲዎች እዚያዉ ጫካ ዉስጥ ማርክሲዝም ሊኒንዝምን ሲያጠና ያረቀቃቸዉ ፖሊሲዎች ናቸዉ። ከማርክሲዝም ሌኒንዝም መሠረታዊ የፍልስፍና መሠረተ ሃሳቦች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ደግሞ የፖለቲካ ስልጣንን ለመቆጣጠር ኤኮኖሚዉን ተቆጣጠር የሚል ለመሆኑ አንድ ሰሞን ደርሶብናልና ከኛ ከኢትዮጵያዉያን በላይ የሚያዉቅ ያለም አይመስለንም።

ወያኔ በቅርቡ አርቅቆ ለህዝብ ይፋ ያደረገዉን የከተማ መሬት ሊዝ አዋጅ ፍትሃዊና ጤናማ የመሬት ገበያ ለመፍጠር ያስችላል እያለ በነዚያ እሱ ብቻ በሚጨፍርባቸዉ ሬዲዮ፤ ቴሌቪዥንና ጋዜጣ ላይ እየደነፋ ህዝብ አዋጁን እንዲቀበል ለማስፈራራት ሞክሯል። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ከማይገሰሱ የሰዉ ልጆች የተፈጥሮ ነፃነቶች ዉስጥ አንዱ የዜጎች የግል ንብረት የመያዝ መብት መሆኑን በሚገባ ያዉቃል፤ ደግሞም ይህ መሠረታዊ የሆነ የዜጎች መብት እየተረገጠ እንኳን ስለ አገር እድገትና ልማት በወጉ ደረቅ እንጀራ በልቶ ስላማደርም ማዉራት እንደማይቻል  የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ካወቀ ቆይቷል። ደግሞስ መሬትን ጨምሮ አብዛኛዉ የአገሪቱ ንብረት በህወሀት ፓርቲ አባላትና በጥቂት የአንድ ዘዉግ አባላት ብቻ በተያዘበት አገር እንኳን "ነፃ ገበያ"  ገበያ የሚባል ነገር እራሱ እንዴት ሊኖር ይችላል?  ነፃ ገበያ ማለት ዜጎች በነፃነት በሚኖሩበት አገር ማንም ጣልቃ ሳይገባባቸዉ ዕቃና አገልግሎትን እየተለዋወጡ በጋራ የሚያድጉበት የኤኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብ እንጂ መለስ ዜናዊ ላሰኘዉ ህጋዊ ሽፋን እየሰጠ ያላሰኘዉን ደግሞ እጁን እያሰረ አንዱን ኃብታም አንዱን ደሃ የሚያደርግበት የመርገም ስርዐት አይደለም።

የኢትዮጵያ ገበሬ ለብዙ አመታት ለመኳንንቱ፤ለባላባቱና ለጭቃ ሹም የላቡን ዉጤት እየገበረ ኖሯል። በዚህ ስርዐት ዉስጥ መኳንንቱ ሰርግና ምላሽ እየደገሰ ደሃዉን ገበሬ የመለማኛ መሳሪያዉ አደርጎት ቆይቷል። ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ይህንን አስከፊ የሆነ ስርዐት ለመቀየር ፈቃደኛ ያልነበሩት የሳቸዉ ስርዐት ከፊዉዳሉ የመሬት ይዞታ ዉጭ በራሱ መኖር እንደማይችል ስለሚያዉቁ ነበር። ዛሬም እድገት፤ ትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ግድብ እየተባለ ብዙ ቢተረክም አገራችን ኢትዮጵያ አንድ በልቶ የጠገበን ከሃዲ በሌላ ለመብላት አፉን በከፈተ ከሃዲ ከመተካት ዉጭ ህዝብ አሜን ብሎ የተቀበለዉ የስርዐት ለዉጥ ማየት አልቻለችም። ዛሬ በግልጽ በግልጽ እንደምናየዉ የቀድሞዎቹ የፊዉዳል መኳንንት በአሁኖቹ የወያኔ ሹማምንት የቀድሞዎቹ የፋብሪካ ከበርቴዎች ደግሞ በዛሬዎቹ የኤፎርት ባለንብረቶች ተተክተዋል። በፊዉዳሉ ስርአት ዉስጥ የራሰቸዉን ህዝብ ሰጥ ለጥ ብሎ ለገዢዎች ሰግዶ እንዲኖር ያስገድዱት የነበሩት ባላባትና ምስለኔዎች በዛሬዎቹ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን፤ ግርማ ብሩን፤ ሽፈራዉ ሽጉጤን፤ አዲሱ ለገሰንና ሬድዋን ሁሴንን በመሳሰሉ ወዶ ገባ ምስለኔዎች ተተክተዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ ኢፍትሃዊ አገዛዝ ያንገሸገሸው መምህር የኔሰው ገብሬ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መምህር የኔሰው ገብሬ እፍትሃዊነትን በመቃወም በራሱ ላይ እርምጃ በወሰደበት ሰ ዓት እስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች እንደገለጹት መምህሩ የወረዳና ዞን ምክር ቤት ሹሞች ስብሰባ ከሚያካሂዱበት ቦታ ሂዶ ወያኔ በአገራችንና በህዝባችን ላይ የሚፈጽመውን ግፍና መከራ እየተመለከትኩ መኖር ስልችቶኛል እያለ በራሱ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ በማቃጠሉ ወደ ዋካ ሆስፒታል ለህክምና እርዳታ ቢወሰድም ክፉኛ በመጎዳቱ ህይወቱ ሊተርፍ እንዳልቻለና ባለፈው ሰኞ ህይወቱ አልፎ በማግሥቱ ማክሰኞ ህዳር 5 እንደተቀበረ ገልጸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የተነሳውና እስካሁንም ውጥረቱ ያልረገበው የዋካና አካባቢው ህዝባዊ አመጽ አሁንም ባለበት መልኩ እንደቀጠለ መሆኑንና በአካባቢው የተሰማራው ልዩ ሀይል  አሁንም ከስፍራው አለመልቀቁን ዘጋቢያችን ከአካባቢው ያሉ እማኞችን በስልክ በማነጋገር በላከልን ሪፖርት ገልጾአል።

ቀደም ብሎ በዋካ ከተማ ከተነሳ  መብት ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ የተደረገውን የተቃውሞ ሰልፍ ተከትሎ "የህዝቡ ጥያቄ ፍትሐዊ ቢሆንም፣ የወያኔ አገዛዝ ግን አስፈላጊውን መልስ ሊሰጥ አልቻለም" በሚል ምክንያት፣ የቶጫ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረው ፈቃዱ ወልደሩፋኤልና  ፤ የዞኑ አቃቢ ህግ የሆነው  ከበደ ካሳ በራሳቸው ፈቃድ ስልጣናቸውን መልቀቃቸውን ኢሳትን መዘገቡ ይታወሳል።

ይህ በዚህ እንዳለ በዘረኛው ወያኔ ኢፍትሃዊ አገዛዝ በመማረር እራሱን በኢሳት ያጋየው ወጣት የኔሰው ገብሬ አሟሟት ዜና በአገሪቱ ውስጥ እንዳይሰማ ለመከላከል ከዋካ ዞን ጋር  የሚያገናኝ የስልክ መስመር በትክክል እንዳይሰራ መደረጉ  ታወቀ።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በመላው አገሪቱ በዘረጋው ኢፍትሃዊነት በሙስናና በስልጣን ብልግና የተጨማለቁ የዞን አስተዳዳሪዎች በህዝብ ላይ እያደረሱ ያሉትን እስራትና ወከባ በመቃወም ባለፈ አርብ ህዳር 1 ቀን እራሱን በ እሳት ያጋየው ወጣት መምህር የኔሰው ገብረ ዜና በመላው አገሪቱ እንዳይሰራጭና ህዝባዊ ተቃውሞ እንዳይቀሰቅስ ስጋት የገባው የወያኔ ባለሥልጣናት የዋካ ዞን የስልክ መስመር መዝጋታቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

ወጣት የኔሰው ገብሬ በራሱ ላይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት በዳውሮ ወረዳ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ በሃይል ለመጨፍለቅ ሲባል የታሰሩ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱና ህዝብ ላነሳው ጥያቄ ተገቢው ምላሽ እንዲሰጥ ከክልሉና ከዞኑ ተወጣጥቶ በመስተዳድሩ ጽ|ቤት ስብሰባ ላይ ለነበረው የወያኔ ተላላኪዎች ቡድን ጥያቄ አቅርቦ እንደነበረ የተናገሩት የግንቦት 7 ምንጮች ፤ በአጸፋ ከባለሥልጣናቱ ለተሰጠው ትዕቢታዊ ምላሽ “ፍትህ እና ነጻነት በሌለበት አገር ከመኖር ሞት ይሻላል እያለ በራሱ ነዳጅ እርከፍክፎ ክብሪት ስጨር በስርዓቱ ላይ የተንገፈገፉ ሚሊዮኖች አርማውን አንስተው እራሳቸውን ነጻ እንደሚያወጡ ጮክ ብሎ በእርግጠኝነት እየተናገረ እንደነበር ገልጸዋል።

የዚህ ዜና በአገርና በውጪ መዛመት ሊያስከትለው የሚችለውን መዘዝ የተገነዘበው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፤ የኔሰው ገብሬ ህይወት ካለፈበት ካለፈው ሰኞ ጀምሮ ይህ ዜና እስከተጠናከረበት ቀን ድረስ የዋካ ዞን ስልኮች ሆን ተብሎ መልዕክት እንዳይቀበሉ መደረጋቸውን ዘጋቢያችን ማረጋገጡን ገልጾአል።

በቱኒዚያ ለተቀሰቀሰውና እንደሰደድ ኢሳት በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ለተሰራጨው የጻረ አምባገነኖች ህዝባዊ አመጽ ዋናው ምክንያት፤ ሞሃመድ ቡአዚዚ የተባለ አንድ ቱንዚያዊ ወጣት “የግፍ አገዛዝ ይብቃ” በሚል በራሱ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ ማቃጠሉ ዜና በመላው አገሪቱና ከዚያም በላይ በአለም መሰራጨቱ የቀሰቀሰው ቁጣ እንደሆነ ይታወቃል።

ቱኒዚያዊው ሞሃመድ ቡአዚዚ በራሱ ላይ በፈጸመው ቃጠሎ ሆስፒታል ገብቶ በነበረበት ወቅት የወቅቱ አምባገነን ፕሬዝዳንት የነበሩት ዚን እልአቢዲን ቤን አሊ ሆስፒታል ድረስ ሂዶ ጎብኝቶት እንደነበረና የቀብር ሥነሥርዓቱም በደማቅ ሁኔታ እንዲፈጸም ፈቅዶ እንደነበረ ሲታወቅ፤ የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ግን ህዝብ ለማፈን በዋካ ዞን የመደበው የፌደራል ፖሊሲ ሆስፒታል በር ላይ በማቆም የየኔሰው ህይወቱ እስኪያልፍ ዘመድ ጓደኛ እንዳይጎበኘው ከመከልከሉም በላይ ህይወቱ ካለፈ ቦኋላ የቀብር ሥነሥር ዓቱ ላይ ማንም እንዳይገኝ እንዳደረገ የግንቦት7 ዘጋቢ አረጋግጦአል።

ወያኔ የስልክ ግንኙነት ለማወክ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም አንዳንድ መረጃዎች አፈትልከው እየወጡ በመሆናቸው  ከመምህር የኔሰው ገብሬ ሞት በሁዋላ የአካባቢው ወጣቶችን መረጃዎችን ለውጭ አገር የመገናኛ ብዙሀን ሰጥታችሁዋል በሚል እየተዋከቡ መሆናቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል። ወያኔ ዜናው እንዳይዛመት ለመከላከል የስልክ መስመሮችን  ሆን ብሎ እያወከ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወያኔን የሰብ አዊ መብት ጥሰቶችንና ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎችን የማዋከብ ዘመቻ በማስረጃ እያጋለጠ ያለው የቢቢሲ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ቢሮን ጨምሮ ሌሎች የአለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀን የመምህር የኔሰው ገብሬን አሟሟት ሰፊ የዜና ሽፋን መስጠት መጀመራቸው ታውቆአል።

ኢፍትሃዊነትን ተቃውሞ የገዛ ህይወቱን በ እንዲህ አይነት ጭካኔ የቀጠፈው የኔሰው ገብሬ የወያኔ አገዛዝ አሰቃቂነት አመልካች መሆኑን ከህዝብ እየደረሱ ያሉ አስተያየቶች ያመለክታሉ።

ነጻነትና ፍትህ ፈላጊው የኢትዮጵያ ህዝብ የዚህን ወጣት አርበኛ አርማ በማንሳት በክብር መሞት ነጻነት ከሌለው ህይወት የሚመረጥ መሆኑን ለፋሽስቱ መለስ ዜናዊና በዙሪያው ለተኮለኮሉት ራስ ወዳዶች ማሳየት ይኖርበታል።

## በዋካ ከተማ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

"መንግስት በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ምን አገባው”፣ የሚል ጥያቄ እንዳነሳና በጽኑ እንደተቃወመው ኢሳት የዘገበ ሲሆን አቶ ተፈራ ታደሰ የተባሉ አማኝ ጥቅምት 14 ከቤተክርስቲያኒቱ  ግቢ በፖሊስ ታፍነው ሲወሰዱ ምንም ተቃውሞ ያላሰሙ የአካባቢው ሃላፊዎች ቤተክርስቲያኑዋ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ለፖለቲካ አላማቸው ማራመጃ የ እምነት አባቶችን ማጥቃት መጀመራቸው ክፉኛ እንዳስቆጣቸው እናም በዚህም ምክንያት ተቃውሞ ማሰማታቸውን ገልጾአል።

ወያኔ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለፈጣሪያቸው ሳይሆን ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ታማኝ የሆኑትን የፖለቲካ ወገናዊነት ያላቸውን ሰዎች በመሾም ህብረተሰቡ በአምልኮ ቦታ እንዲወዛገብና እንዲጋጪ ሲያደርግ እንደነበረ በተከታታይ ሲዘገብ የነበረ መሆኑ ይታወቃል። ለዘመናት አብሮ የኖረውን የክርስትናና የሙስሊም እምነት ተከታዮችን እርስ በርስ ለማጫረስ በተለያዩ ቦታዎች ሲፈጸም ከኖረው ተንኮል በተጨማሪ በቅርቡ ሙስሊም ህብረተሰብ ለሁለት ጎራ በመከፈል በመካከላቸው ግጭት እንዲነሳ ለማድረግ የወያኔ ሹሞች በግልጽ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## ሲረገጥ የሚታገስ ሲጫኑት የሚሸከም መሬት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የአፄ ኃ/ሥላሤ ስርዐት ከፊዉዳሉ የመሬት ግኙኝነት ዉጭ መኖር እንዳልቻለ ሁሉ የመለስ ዜናዊ ስርዐትም መሬትን ጨምሮ የአገሪቱን ዋና ዋና ኃብት ካልተቆጣጠረ መኖር እንደማይችል በሚገባ ያዉቃል፤ ስለዚህም ነዉ የገጠሩ መሬት አልበቃ ብሎት የከተማዉንም መሬት የግሉ ለማድረግ ጎንበስ ቀና ማለት የጀመረዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ሃያ አመት ሙሉ መሬቴን ስጡኝ ብለህ ብትጮህም መለስ ዜናዊ ግን የመሬትን ጉዳይ አታንሱብኝ ብሎ ጭራሽ የመሬት ይዞታን ህገ መንግስቱ ዉስጥ ሸጉጦት መሬቴን ብሎ የጠየቀን ሁሉ በህገ መነግሰቱና በህግ መንግሰታዊ ስርዐቱ ላይ የተነሳ ጠላት ነዉ እያለ ሲያስርና ሲገድል ቆይቷል። ዛሬ በግልጽ እንደምናየዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት የመንግስት ንብረት መሆኑ የጠቀመዉ የኢትዮጵያን ገበሬ ሳይሆን የወያኔን ገዢ መደብ አባላትና የህንድ፤ የቻይናና የሼክ መሐመድ አላሙዲንን ኩባንያዎች ብቻ ነዉ። በቅርቡ ከወደ ጋምቤላ እንደተሰማዉ ደግሞ የጋምቤላን ገበሬ ህይወት ይለዉጣል ተብሎ አገር የሚያክል ትልቅ መሬት የተሰጠዉ ካራቱሪ የሚባል የህንድ ኩባንያ አገራቸዉ ዉስጥ መሬት አጥተዉ የተቸገሩ የህንድ ገበሬዎችን በብዛት አስመጥቶ የእርሻ ስራ ለመጀመር ዝግጅቱን ጨርሷል። ይህንን ለማወቅ ደግሞ ጠንቋይ መቀለብ የሚያስፈልግ አይመስለንም። በለምለምነቱ የታወቀዉን የጋምቤላ፤የኦሮሚያና የቤንንሻንጉል ክልል መሬት በዘመናዊነት ስም ለህንድ ኩባንያዎች የሸለመዉ መለስ ዜናዊ የከተማዉን መሬት ደግሞ በእንዱስትሪ ዘመናዊነት ስም ለቻይና መሸለሙ የማይቀር ይመስላል። መለስ ዜናዊ እጅና እግሩን ስላሰረዉ ብቻ እራሱን መቀለብ የተሳነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የሁሉም ነገር ቁልፍ የሆነዉን የፖለቲካ ሥልጣን ለወያኔ፤ የገጠሩን መሬት ለህንድ የከተማዉን መሬት ደግሞ ለቻይና ሰጥቶ እሱ እራሱ እንዴት እንደሚኖርና ምን ላይ እንደሚኖር ካሁኑ ለይቶ ካላወቀ መጪዉ ዘመን ያበቃለት የባርነት ዘመን መሆኑን ካሁኑ እንዲገነዘበዉ አደራ እንላለን።

“የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነዉ” እንደሚባለዉ ወያኔ እስከዛሬ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ዬት እንዳደረሱንና ዛሬም እየወሰደ ያለዉ እርምጃ ወዴት እንደሚወስደን በሚገባ የተገነዘብን ይመስላል። የወያኔ ጥረት በአንድ በኩል ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ወያኔያዊ ስርአቱ እንዲቀጥል ማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እሱ እራሱ ሆን ብሎ የፈጠራቸዉን ተቋማት በመጠቀም በገጠርና በከተማ ለወያኔ ስርዐት ታማኝ የሆኑና በስርአቱ ላይ ምንም አይነት ጥያቄ የማያነሱ የባለንብረቶች መደብ መፍጠር ነዉ። ይህንን ዕቅዱን ደግሞ ታዛዥ ለሆነና የፖለቲካ ፍላጎት ለሌለዉ የባዕድ ኃይል በገጠሪቱ ኢትዮጵያ  ሰፋት ያለዉ ትልቅ መሬት በመስጠትና የኢትዮጵያን ገበሬ ከመሬቱ ነጥሎ የዚህ ባዕድ አካል ጥገኛ በማድረግ ተግባራዊ እያደረገ ነዉ።

ወያኔዎች ለእኛ መብትና ነፃነት የሚታገሉ ወንድሞቻችንን የዘር አካል እንደ ፊኛ ሲያፈነዱ፤ የሴቶች እህቶቻችንን ጡት እንደ ገመድ እየጎተቱ ሲያሰቃዩና ለምለም መሬታችንን ለባዕዳን ሲሸጡ ምንም ያደረግነዉ ነገር ባለመኖሩ የልብ ልብ ተሰምቷቸዉ ዛሬማ ጭራሽ ከተሜዉን በገዛ መሬቱ ላይ ገባር ሊያደርጉት ነዉ። እነ መለስ ዜናዊ እስከዛሬ የበደሉን አልበቃ ብሏቸዉ ዛሬማ “ምናባታቸዉ ይሆናሉ” በሚል ንቀት ተወልደን ለወግ ማዕረግ የበቃንበትን መሬት ከኛ ቀምተዉ እነሱ በአምሳያቸዉ ለፈጠሩት ባለኃብት ሊያከፋፍሉ ነዉ። አባቶቻችን ጅላጅል ልጅ የአባቱን መሬት በባለጋራ ሲያስቀማ “የልጅ ደንጋዛ የአባቱን መሬት ያጋዛ” ይሉ ነበር። የዚህ ዘመን ትዉልድ የሆንከዉ ኢትዮጵያዊ ወገናችን ሆይ ይህንን መለስ ዜናዊ የደገሰልህን ድግስ ከነመሶቡ ካልገለበጥከዉ የሚጠብቅህ ዕጣ ሳትወድ በግድ የእናትና አባትህን መሬት የወያኔ ከበርቴ ሲገዛዉ ቆሞ መመልከት ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያዉያን እትብታቸዉ በተቀበረበት እናት አገራቸዉ ውስጥ ይቅርና ተሰድደዉ በሚኖሩበት የባዕድ አገር ዉስጥም ቢሆን በፍጹም ሊቀበሉት የማይገባ ለልጅ ልጆቻችን የሚተላለፍ ሐፍረት ነዉ።

ባለፉት ሃያ አመታት ስለ መለስ ዜናዊ ካወቅናቸዉ ብዙ ነገሮች ዉስጥ አንዱ መለስ ዜናዊ የለየለት ቂመኛ ሰዉ መሆኑን ነዉ። ይህ ቂመኛ ሰዉ ጥርሱን ከነከሰባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የከተማዉ ነዋሪ ህዝብ ነዉ። መለስ ዜናዊ ከተሜዉን በተለይም የአዲስ አበባን ከተማ ነዋሪዎች የሚኮንነዉ አንድም በፍራቻ አንድም “እንዴት ተደፈርኩ” ከሚል የቂም በቀል መንፈስ በመነሳት ነዉ። መለስ ዜናዊን እጅግ ካስደነገጡትና ሁሌም በፍርሃት ተሸብቦ እንዲኖር ካደረጉት ክስተቶች አንዱ የአዲስ አበባ ህዝብ “ሱናሚ” እያለ የሚጠራዉና ሚያዝያ 30 1997 ዓም ቅንጅትን በመደገፍ የተካሄደዉ ታላቅ ሠላማዊ ሠልፍ ነዉ። ካይሮ ጣሂሪር አደባባይ ላይ የተካሄደዉን ህዝባዊ ቁጣ የተመለከተዉ መለስ ዜናዊ የ1997ቱ ሱናሚ እንዳይደገም የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። ከነዚህ እርምጃዎች ዉስጥ አንዱ የከተማዉን ነዋሪ መሬት ቀምቶ ከተሜዉ ጧትና ማታ እጅ እየነሳ የሚኖር ጥገኛ እንዲሆን ማድረግ ነዉ። ይህ ከሰሞኑ ጆሯችን ዉስጥ የገባዉ የከተማ መሬት አዋጅ ተግባራዊ ሲሆን ደግሞ መለስ ዜናዊ ጋምቤላ ዉስጥ ካሳየን “ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል” መብትና ነፃነታችንን የምናስከብረዉ፤ እንደ ሰዉ በአገራችን ተከብረን የምንኖረዉና ልጆቻችንን አሳድገን በሠላም የምንጦረዉ ይህ ሁሉ እንዳይሆን እንቅፋት የሆነብንን የመለስ ዜናዊን ስርዐት ሌሎች እንዳደረጉት ሁሉ እኛም በቃ ብለን በህዝባዊ አመፅ ስናስወገወድ ብቻ ነዉ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ**
**እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org